# የቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠና

## የመርሃግብሩ መሰረታዊያን

### -----------መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስትሪስ------------

የቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠናን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ አምስት አስፈላጊ ግብአቶች አሉ፤ እነዚህ ግብአቶች መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ አገልግሎት የሚጠቀምባቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የትኩረት አቅጣጫዎች፡- ራዕይ፣ ሞጁላር ስልጠና፣ የስልጠናው ግብአት ይዘት፣ ክትትል እና ድጋፍ፣ እንዲሁም ምዘና ናቸው፡፡ በቤተክርስቲያን ተከላ አገልሎት ላይ የተሰማሩ ግለሰብ በመጋቢው የድጋፍ፣ ይሁንታ እና በቃለ መጠይቅ ከተገመገመ በኋላ እነዚህ አምስት የቤተክርስቲያን ተከላ ግብአቶች ቤተክርስቲያኒቱን ለማባዛት አስፈላጊ መሆናቸው ይረጋገጣል፡፡

1. ቤተክርስቲያን የመትከል ራዕይ የተሳካ የቤተክርስቲያን ተከላን መደገፍ የሚፈልጉ ድርጅቶች እና መሪዎች ከልብ የመነጨና  በድርጊት የተደገፈ ራዕይ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ቤተእምነቶች እና ማህበረ ምዕምናን ቤተክርስቲያን ተከላ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ሕይወት ለመለወጥ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ እንደሆነ ግንዛቤው አላቸው፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ የቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠና የሰጠናቸውን ሰዎች አገልግሎት በማጥናት ያገኘነው መረጃ እንደሚያመለክተው፤ የቤተክርስቲያን ተከላ ራዕይን ተቀብለው የራዕዩው ተካፋይ ሆነው የሚሰሩ መሪዎች ያሉት የቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ በአገልግሎቱ ውጤታማ ይሆናል፤ የሚያዘልቀውንም አቅም ያገኛል፡፡ በተቃራኒው ከቃል የዘለለ ድጋፍ የሌለው የቤተክርስቲያን ተከላ ራዕይ በተስፋ መቁረጥ እና ከንቱ ልፋት ይደመደማል፡፡ ግልጽ የሆነ እና በመንፈስ የሚመራ ራዕይ ቤተ እምነት ወይንም ማህበረ ምዕምናን እንዲበዙ እና አዳዲስ አማኝ ማህበረሰብ ህብረቶች እንዲመሰረቱ ያደርጋል፡፡
2. ሞጁላር ስልጠና

ሞጁላር ስልት መሰረቱን ያደረገው ትግበራ እና ክንውንን በመተንተን ላይ ሲሆን በእያንዳንዱ ሞጁል ማብቂያ እና የቀጣዩ መጀመሪያ የተግባር ስልጠና እንዲያደርግ የሚያስችል መመሪያን ያካተተ ነው፡፡ የአለም አቀፉ የላብ አደሮች ድርጅት ሞጁላር ስልጠናን እደሚከተለው ይተረጉመዋል “ሞጁላር ስልጠና የሰልጣኙን ፍላጎት፣ ስልት ማጎልበት፣ ወይም ሙያዊ መዋቅርን ማዕከል በማድረግ የተለያዩ ሞጁሎችን ወይም ክፍለ ትምህርቶችን በማዋሃድ አንድ ፕሮገራም በመፍጠር ስልጠናው በየጊዜው አዳዲስ አሳቦችን ለማቀፍ እንዲያስችል ታስቦ የሚዘጋጅ የስልጠና ስርአት ነው፡፡” በሞጁላር ስልተ ትምህርት የሚሰጥኑ ደረጃ በደረጃ

የሚያድግ ዕውቀት  ያገኛሉ፡፡ በእርግጥ አንዳንዶች ሞጁላር ስልጠናን “ወቅቱን የጠበቀ ስልጠና” ብለው ነው የሚጠሩት፤ ምክንያቱም የስልጠናው ተሳታፊዎች በእያንዳንዱ ስልጠና ማብቂያ የተግባር ልምምድ ስለሚያደርጉ፤ በትግበራ ወቅት የተከሰቱትን በሪፖርት መልክ ስለሚያቀርቡ፡፡

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ ሚኒስትሪስ ስለ ትምህርት ለአስራ ሁለት ወር በድምሩ 100 ሰዓታት የትምህርት ጊዜ ያለው የቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠና ነው፡፡ በአብዛኛው ይህ ስልጠና በወር አንድ ሙሉ ቀን የሚሰጥ ሲሆን በዚህ ስልጠና አምስት ርዕሶች ይዳሰሳሉ፡፡ ከአንድ ቀን ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች እስከ ቀጣዩ ስልጠና ቀን ድረስ ለአንድ ወር ወደ ተግባራቸው ይመለሳሉ፡፡ ከላይ ለማብራራት እንደተሞከረው ሞጁላር ስልጠና የሚጠቀመው ሰልጣኞች አንድ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ እንዴት አድርገው ቤተክርስቲያን ማስፋፋት እና ማጎልበት እንደሚችሉ ለማወቅ የሚረዱ ጥያቄዎችን በተግባር ሲያውሉ የከበዳቸውን ማንኛውንም ጉዳይ ይዘው እንዲመጡ እድል ስለሚሰጥ ነው፡፡ በዚህ ሚኒስተሪ የተዘጋጁ ሞጁሎች በቀላሉ ሲታወቁ እና ሲተገበሩ ከሚችሉ ጉዳዮች ወደ ከባድ እና ውስብስብ ጉዳዮች እንዲሄድ ተደርጎ የተሰደረ ነው፡፡ የዚህ ተግባር ተኮር ስልጠና ጠቃሚ የሚሆነው ቤተክርስቲያን መሪዎች እና በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ጥቂት ፋታ ወስደው እንዲማሩ እና አሁን ያለው የቤተክርስቲያን እድገት ምን እንደሚመስል እንዲገነዘቡ እድል መስጠቱ ነው፡፡ የሰልጣኞች በተደጋጋሚ መገናኘት አንዱ ሌላውን እንዲያበረታታ እና አንዱ ለሌላው ግልጽ እንዲሆን እድል ይፈጥራል፡፡ ይህም ቤተክርስቲያን ለማብዛት በእጅጉ ይጠቅማል፡፡

3. የመጽሐፉ ይዘት

የዚህ ስልጠና ሂደትን እንደ አንድ ስርአተ ትምህርት ማየት አይገባንም፤ ምክንያቱም ከስርአተ ትምህርት በላይ ስለሆነ፡፡ አንዳንድ ስልጠናዎች አብዛኛውን የስልጠና ሃሳብ በስርአተ ትምህርት ግንባታ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያለው አውድ እንዲኖረው ያደርጋሉ፡፡ የዚህ ስልጠና ስለት አንዱ ስልጠና አልቆ ሌላውን ለመጀመር በሚከናወኑ ተግባራዊ ድርጊቶች እና በዚያ ከሚገጥሙ ፈታኝ ሁኔታዎች እና መልካም አጋጣሚዎች ላይ ትኩረት የሚሰጥ ነው፡፡ እነዚህ በስልጠና ወቅት የሚገኙ ልምዶች በሞጁል ከተካተተው ይዘት እኩል ለቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ክህሎት መዳበር አስተዋጾ አላቸው፡፡

በኤም.ኤን.ኤም የስልጠና መጽሐፍት ውስጥ ያሉ ጭብጦች በልዩነት የኤም.ኤን.ኤም ብቻ አይደሉም፡፡ በዚህ የተካተቱትን ጭብጦች እንደ አንገት ጌጥ ማጫወቻ መውሰድ እንችላለን፤ ምንም እንኳን የአንገት ጌጡ በሁሉም አንገት ላይ የሚገኝ ቢሆኑም የማጫወቻዎቹ ቅርጽ ይለያያል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጭብጦች በኤም.ኤን.ኤም የስልጠና ማኑዋል ውስጥ ብቻ የሚገኙ ናቸው፡፡

ሀ. አውዱን የጠበቀ ስርአተ ትምህርት፡- የኤም.ኤን.ኤም ማኑዋል በሶስት መሰረታዊ ምህዋሮች ላይ አንዲዞር ሆኖ የተሰራ ነው፤ ግለሰብ፣ መልዕክት እና የማስተማር ስልት፡፡ ግለሰብ የሚለው የመጀመሪያው ግብአት ቤተክርስቲያንን በመትከል ስራ ላይ የተሰማራን ሰው መንፈሳዊ እና ክህሎታዊ አቅምን በስልጠናው ውስጥ በማስፋ እንዲያዳብር የሚያግዝ ነው፡፡ ሁለተኛው ግብአት (መልዕክት) ደግሞ የወንጌልን መልዕክት ጭብጥ እና እንዴት ይህን እውነት ለሌሎች ማቅረብ እና ምሳሌ መሆን የሚያስችል እንዲሆን ማዘጋጀት ነው፡፡ ሶስተኛው ጭብጥ (የማስተማር ስልት) ደግሞ ቤተክርስቲያንን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ ለማየት እና ለመረዳት የሚያስችል የማህበረሰቡን አውድ በጥልቀት ለማሳየት እና ሰፊውን ባህል ተደራሽ ሊያደርግ የሚችል ወንጌልን የመስበክ ጥበብ ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ በስልጠናው ማገባደጃ የሚሰጡት ስልጠናዎች እንደ ደቀመዛሙርትን ማፍራት፣ እንደ ቤት ህብረት ያሉ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ቡድኖችን መምራት እና የማህበረሰብን ፍላጎት ማወቅ እና ማገልገል ከፍ ያለ ክህሎት የሚጠይቁ ጭብጦችን ያካተቱ ናቸው፡፡

ለ. የአተገባበር ክህሎትን ማዳባር፡- በዚህ ስልጠና ወቅት ለጭንቅላት ዕውቀት ብቻ የሚሆን መረጃ ወይንም እዲህ ያለውን ዕውቀት የሚያዳብር የትምህርት መርጃ አይደለም የምንለግሰው፤ ነገር ግን ትኩረታችን የቤተክርስቲያን ተከላን የሚያፋጥን እና የአተገባበር ክህሎትን የሚያዳብር፤ ጥናት እና ምርምርን እንዴት ማድረግ እና ከቤተክርስቲያኒቱ አባላት ብዛት አንጻር እንዴት መተንተን/ መተርጎም እደሚቻል፣ ማህበረሰቡ እንደሚያስፈልገው በጥብቅ የሚያምንበትን ፍላጎት ማገልገል፣ አዳዲስ ቁልፍ ሰዎችን መተዋወቅ፣ አውዱን ጠብቆ ወንጌልን ማቅረብ፣ አነስተኛ የሰው ቁጥር ያለው የቡድን ጥናት መምራት፣ ግጭትን መፍታት፣ አዳዲስ መሪዎችን ማሰልጠን፣ የአምልኮ ፕሮግራሞችን መምራት፣ በቡድን መስራት፣ መስበክ፣ ለውጥ ሲያመጡ የሚችሉ ዕቅዶችን ማርቀቅ እና ለእያንዳንዱ ጉዳይ የሚሆንን የበጀት ዕቅድ ማዘጋጀት፡፡

የአተገባባር ክህሎት የሚገለጡት ከሰዎች ጋር በምንሰራበት ወቅት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- በቤተክርስቲያን ተከላ የተሰማራ አገልጋይ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎች /Inductive Bible study/ መምራትን ቢማር፤ በዚህ ውስጥ እንዴት አድርገው ክፍሉን ማጥናት እንዳለባቸው እና እንዴት አድርገው ጥናት ማዘጋጀት እንዳለባቸው ይማራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ በቡድኑ የታቀፉ አባላት ክፍሉን እንዲረዱ የሚያደርጋቸውን ጥያቄ በማዘጋጀት ጥናቱን በአጥኚዎቹ ዘንድ መተግበር የሚያስችል ጥናት እዲሆን ያደርጋል፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው አገልጋይ የተማረውን የሚለማመድበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥርለታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቡድን አባላቱና ፕሮግራሙን የሚያስተባብረው ግለሰብ ምን አይነት ክህሎት በበለጠ ማዳበር እንዳለበት በወንድማዊ ፍቅር እና ነጻነት በመልካም ቃላት ይጠቁሙታል፡፡ እንዲህ ያለውን ስልጠና በተደጋጋሚ በሚዘጋጁ ማኑዋሎች የክህሎት ማጎልበቻ ስልጠና እንዲወስድ ማድረግ በቤተክርስቲያን ተከላ የተሰማራውን አገልጋይ ውጤታማ የሚያደርግ መሰረታዊና አስፈላጊ ስልጠና ነው፡፡

ክህሎትን የሚዳብር ስልጠና ነገሮችን ለረጅም ጊዜ ከመሰረታቸው ጀምሮ በማጥናት እና በየጊዜው የሚገጥመውን ሁኔታ ማጥናትን የሚያካትት ነው። በቅደም ተከተል የሚቀርቡት የክህሎት ማዳበሪያ ስልጠናዎች ከአንዱ ወደ ሌላው ሲጨምር አገልጋዩ እነዚህን ተግባራዊ የሚያደርግበት አቅም ይጠናከራል። ለምሳሌ አገልጋዮች ሌሎችን ለማሰልጠን በሚወስዱት ስልጠና ውስጥ ሌሎች ሰዎችን መተዋወቅ የሚችሉበት ክህሎት እየዳበረ ይመጣል።

መ. የትግበራ እቅዶች፦ እያንዳዱ ስልጠና የሚጠናቀቀው በቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋዮች ወይም የቤተክርስቲያን መሪዎች የትግበራ እቅድ እንዲያዘጋጁ በማድረግ ነው። የእያንዳንዱ ቀን ትምህርት የሚጠናቀቀው “ቀጥሎ ምን መስራት ይጠበቅብኛል?” ወይም “አሁን ምን ማድረግ አለብኝ?” የሚሉ ጥያቄዎችን በመመለስ ነው። ታዲያ ይህ የትግበራ እቅድ በስልጠና ወቅት ለሰልጣኞች በሙሉ የሚቀርብ ሲሆን እያንዳንዱ ሰልጣኝ አንዱ የሌላውን እቅድ ስለሚያውቅ እርስ በእርስ ለመበረታታት እና ተጠያቂነትን ለመፍጠር የሚያግዝ አጋጣሚ ይሆናል።

ሰ. ምልከታ እና ማዛመድን መሰረት ያደረገ የጥናት ስልት፦ ለዚህ ስልጠና ተመራጭ የሆነው ስልት ጥያቄ ማንሳት እና ሰልጣኞች ጥያቄውን በትናንሽ ቡድኖች ሆነው እዲመልሱት ማበረታታት ነው። ስልጠናው ውይይትን እና ማዛመድን ለቡድን ከማቅረብ ጋር በመቀላቀል የሚቀርብ ቢሆንም ምልከታ እና ማዛመድ ከምንም በላይ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ይሆናል። ምክንያቱም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን እንዴት እንደሚመራ ለማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ ስላለው። የቡድን ውይይቱ የሚካሄደው አንድ ልምድ ያለው መምህር የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን መሰረት በማድረግ ካስተማረ በኋላ ይሆናል።

ረ. ሁሉን አቀፍ የማህበረሰብ ተግባር፦ በስልጠናው ወቅት እያንዳንዱ ሰልጣኝ እዴት አድርጎ ማህበረሰብ አቀፍ ተግባርን የስልጠናው አካል ማድረግ እንዳለበት ይገነዘባል። እንደ ቤተክርስቲያን ተከላ አገልጋይ የተሰማራበትን አካባቢ ማህበረሰብ አኗኗር በማጥናት የማህበረሰቡን ፍላጎት ማወቅ ይችላል። በዚህ መርሃ ግብር ተካፋይ የሚሆኑ አገልጋዮች በማህበረሰባቸው ውስጥ ጠልቀው እንዲገቡ የሚያስችላቸው ቁልፍ እቅድ ለማዘጋጀት የሚሆን መርጃ የሚሰጣቸው ሲሆን፤ በዚህም የክርስቶስን ፍቅር በመኖር ማሳየት እንዲችሉ ያግዛቸዋል።

## 4. ድጋፍ እና ክትትል

መልቲፕሊኬሽን ኔትዎርክ አገልግሎት እያንዳንዱ በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራ አገልጋይ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርግ ረዳት እንዲኖረው ያበረታታል። ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርገው ግለሰብ የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ አሊያም መጋቢው የሚሾመው ሌላ አገልጋይ ይሆንና በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው አገልጋይ በሚሄድበት ስፍራ እንደ አጋዥ ሆኖ

ለአንድ አመት ያገለግላል፡፡ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርገው ግለሰብ በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ ከተሰማራው ግለሰብ ጋር በወር አንድ ጊዜ እያንዳንዱ የስልጠና ማኑዋል በተጠናቀቀ ቁጥር መገናኘት ይኖርባቸዋል፡፡ የሚገናኙበት ስፍራ ቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው ግለሰብ ቤተክርስቲያን ለመትከል በሚሰራበት ስፍራ ሲሆን፤ በዚህም ልምድ ለመለዋወጥ እና አብሮ ለመጸለይ የሚሆን አጋጣሚ ይፈጠርላቸዋል፡፡ ሴም.ሴን.ሴም አገልግሎት ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርጉ ግለሰቦች መሰልጠን የሚገባቸውን ጭብጥ ያካተተ የስልጠና ማኑዋል ያዘጋጀ ሲሆን ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርገው ግለሰብ ውጤቱን የሚቆጣጠርበት የጥያቄ አቀጣጫ እና መቆጣጠሪያ ቅጽ ተዘጋጅቷል፡፡ ጥያቄዎቹ ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኩራሉ፤ እነርሱም የግል ሕይወት እድገት፣ የቤተሰብ ሕይወት እና የቤተክርስቲያን ተከላን የተመለከቱ ናቸው፡፡

በዚህ መርሃ ግብር ውስጥ ጠቃሚ ግብአት ተብሎ ሊወሰድ የሚገባው ድጋፍ እና ክትትል የሚሰጠው ግለሰብ አመለካከት ነው፡፡ ድጋፍ እና ክትትል የሚያደርገው ግለሰብ በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራውን አገልጋይ ለማበረታታት እና ውጤታማ ይሆን ዘንድ ለማገዝ እንዲሁም አገልጋዩ በእግዚአብሔር መንግስት ስራ ውስጥ ትርፋማ ይሆን ዘንድ አብሮነቱን ማሳየት የፈቀደ ነው፡፡ የህን መርሃ ግብር በዚህ እንዲካተት ያደረግነው በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው ግለሰብ እንዲያከናውነው የሚጠበቅ ስራ ሳይሆን በአገልግሎቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ አንዲህ ያለው መርሃ ግብር የቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው ግለሰብ የሚጋፈጠውን የብቸኝነት ስሜት የሚቀርፍ ነው፡፡

5. መገምገም

ሴም.ሴን.ሴም ሚኒስትሪ የቤተክርስቲያን ተከላ አገልግሎት ውጤት መገምገም እንዳለበት በጥብቅ ያምናል፡፡ በዚህ መርሃ ግብር ተጠያቂነት ወሳኝ ልምምድ ሲሆን በቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራ አገልጋይ እያንዳንዱ ስኬቱንም ይሁን የገጠመውን ፈታኝ ሁኔታ ማሳወቅ አለበት፡፡ በእያንዳንዱ ሞጁል ማብቂያ በቤተክርስቲያን ተከላ የተሰማራው አገልጋይ ከዚህ በታች እንደተዘረዘሩት ግልጽ መስፈርቶች ወርሃዊ ሪፖርቱን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

- በዚህ ወር ምን ያህል አዳዲስ ሰዎችን ተዋወቅህ/ሽ?
- ምን ያህል ሰዎች ጌታን እንደ ግል አዳኛቸው ተቀበሉ?
- ምን ያህል ሰዎች ተጠመቁ?
- ምን ያህል ትንሽ ቁጥር ያላቸው ሰዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን አቋቋምክ/ሽ?
- በእነዚህ ቡድኖች ውስጥ ምን ያህል ሰዎች አሉ?
- ምን ያህል አዳዲስ መሪዎችን በዚህ ወር ማሰልጠን ጀመርክ/ሽ?
- ምን ያህል ሰዎች አምልኮ ይካፈላሉ (ይህ ቤተክርስቲያኒቱ ከተጀመረች በኋላ የሚመጣ ጥያቄ ነው)?

ከላይ ያነሳናቸው ጥያቄዎች አገልጋዮች ወርሃዊ ሪፖርታቸውን እንዲያዘጋጁ ያግዛቸዋል፡፡ እንዲህ ያለው ጥያቄ “የጠየከውን እና የተቆጣጠርከውን ያህል ውጤት ታገኛለህ” የሚለን የድሮ ንግር የተከተለ ነው፡፡ አገልጋዮቹ ከስልጠና በኋላ፣ በወሩ መጨረሻ ምን እደሚጠየቁ ካወቁ ወሩን ሙሉ ለዚህ መልስ ሲሆን በሚችል ተግባር ላይ ይጠመዳሉ፡፡ (በተጨማሪም “ሪፖርት ማድረግ የሚያስገኛቸው 5 ጥቅሞች” የሚለውን ጥራዝ ተመልከት)

ይህን ጠቅለል አድርገን ስንመለከት፤ ጤናማ ቤተክርስቲያን ተከላ ስልጠና ለማድረግ ከላይ ያነሳናቸው አምስቱ ግብአቶች መካተት አለባቸው፡፡ የእነዚህ አምስት ግብአቶች በስልጠና ውስጥ መካተት ቤተክርስቲያን ተከላ ላይ የተሰማራው አገልጋይ አዲስ፣ የተነቃቃ፣ እና ጤናማ አማኝ ማህበረሰብ ለመፍጠር የወጠነውን እቅድ ከግብ እንዲያደርስ ከፍ ያለ ኃይል ያለው ውህደት ይፈጥራሉ፡፡




የግርጌ ማስታወሻ፡-

ሞጁሎቹ ለሰልጣኞቹ እንደየፍላጎታቸው ሊሰጥ ይችላል፡፡ በከተማ አካባቢ ቶሎ ቶሎ መገናኘት ለምሳሌ በሳምት አንድ ቀን ህብረት ማድረግ ይቻላል፡፡ በአብዛኛው ከሩቅ አካባቢ የሚመጡ ሰዎች በወር አንድ ጊዜ አንኳን መምጣት ስለሚከብዳቸው በሶስት ወር አንዴ ለሶስት ቀናት መገናኘትን ይመርጣሉ፡፡ ለሶስት ቀን ሙሉ እንደ መዝናኛ መሰል የሪፖርት እና የስልጠና ጊዜ ሰልጣኞች እርስ በእርሳቸው እንዲተዋወቁ እና የማይረሳና የሚናፈቅ ጊዜ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

ከዚህ በታች የእኛን አገልግሎት የሚገልጹ ሶስት ዋና ዋና ስልቶችን እንመለከታለን፡-

ሀ. ሳምንታዊ ስብሰባ፡- 48 ሳምንታትን በተከታታይ በሳምንት ለአንድ ምሽት ለአንድ ስልጠና ብቻ፡፡

ለ. ወርሃዊ ስብሰባ፡- በወር አንድ ጊዜ በመሰብሰብ ከ4-5 ስልጠናዎችን በመውሰድ በወር አስራ ሁለት እንዲህ ያሉ ስልጠናዎችን መፈጸም፡፡

መ. በሶስት ወር አንዴ መሰብሰብ፡- በአመት አራት ጊዜ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ተገናኝቶ 12 ስልጠናዎችን መውሰድ፡፡